ኢዜማ

# ለሀገር ሰላም እና ለሕዝብ ደህንነት መከበር መቆማችንን የምንናገረውንም ሆነ የምንሠራውን ሌሎች እንዲወስኑልን ከመፍቀድ እና ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን አሳልፎ ከመስጠት ጋር በፍፁም ሊምታታ አይገባውም!

**ከኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የተሰጠ መግለጫ**

አንኳር

- ኢዜማ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በሙሉ ሰላማዊ፣ ሕጋዊ እና የሌሎችን መብት ባከበረ መልኩ መሆኑ እና ችግሮች በሚያጋጥሙ ጊዜ ወደተካረረ መንገድ ከመሄድ ይልቅ በሰከነ ውይይት ችግሮችን ለመፍታት እንደሚጥርም በተግባር የተረጋገጠ ሀቅ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ኢዜማ ለሀገር ሰላምና አንድነት ከምንም በላይ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚንቀሳቀስ ፓርቲ መሆኑ ይታወቃል፡፡
- ኢዜማ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ወረራ እና ኢፍትሃዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕደላ ጋር በተያያዘ መስከረም 15 ቀን 2013 ዓ.ም ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ለማድረግ ዕቅድ ይዞ ነበር፡፡ በውይይቱ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በመሬት ወረራው ተጎጂ ሆነናል የሚሉ አካላትን፣ የከተማውን ፖሊስ እና የደህንነት አካላትን፣ ከአዲስ አበባ ዙሪያ ያለበቂ ካሣ ተነስተን በስማችን ለሌሎች አካላት ቤቶች ተሰጥተዋል የሚሉ አርሶ አደሮች ነበሩ፡፡
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላም እና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ከመስከረም 15 በኂላ ባሉ ተደራራቢ በዓላት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የሥራ ጫና ውስጥ እንደሚገኝ ባደረሰን ጥቆማ መሰረት ተነጋግረን ውይይቱን ለመስከረም 28፣ 2013 ዓ.ም አስተላልፈናል፡፡ የውይይት ቀን መቀየራችንን ለፀጥታ አካላት፣ ለከተማ አስተዳደሩ እና ለሌሎች የፓናል ውይይቱ ተሳታፊዎች በቁጥር ኢዜማ/036/13 በመስከረም 14 ፣2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አሳውቀናል፡፡
- ይሁን እንጂ በታቀደው ቀን እና ሰዓት ውይይቱን እንደምናደርግ መረጃው የነበረው የከተማው አስተዳደር «የማጥራት ሥራውን አስተዳድሩ ባላጠናቀቀበት ወቅት ውይይት መጥራት ሌላ አተካራ እና ምናልባትም ወደግጭት የሚወስድ በመሆኑ የጠራችሁት ውይይት እንዲሰረዝ እንድታደርጉ እናሳስባለን፡፡» በማለት በደብዳቤ ቁጥር አአ/ከፅ/03/03/23 በከንቲባ ጽሕፈት ቤት በኩል በላከልን ደብዳቤ አሳውቆናል፡፡ ይህ ደብዳቤ እኛ ጋር መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም ከቀኑ 8፡30 ከመድረሱ በፊት አስቀድመው የከተማ አስተዳደሩ ኃላፊዎች ውይይቱን እንድንሰርዝ በስልክ ጥሪ እና በአጭር መልዕክት የተለያየ ሙከራ ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆን ደብዳቤው ሲደርሰን ግን ደብዳቤው ቀድሞ የተጻፈ ለማስመሰል የደብዳቤው ቀን መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም በሚል ነበር፡፡

አንኳር …

- ይህ የከተማ አስተዳደሩ ድርጊት ዓይን ያወጣ ሕገ ወጥነት ቢሆንም እና ውይይቱን የማድረግ ሙሉ መብት እንዳለን ብናምንም አላስፈላጊ ፍጥጫ ውስጥ ከመግባት እና በዚህም ሀገራችን አሁን ካለችበት ውጥረት ላይ ሌላ ውጥረት ከመጨመር ይልቅ ያሉት ሕጋዊ አማራጮችን በመጠቀም መብታችንን ማስከበር እንዳለብን፤ እንዳለብን፤ የሕግ ተቋማትም ያላቸውን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችሉ ዕድል መስጠት አለብን ብለን በማመን ውይይቱን እንደገና ለማራዘም ወስነናል፡፡
- ለሀገር ሰላም እና ለሕዝብ ደህንነት መከበር መቆማችንን እንዲሁም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ የምንወስዳቸው እርምጃዎች የምንናገረውንም ሆነ የምንሠራውን ሌሎች እንዲወስኑልን ከመፍቀድ እና ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን አሳልፎ ከመስጠት ጋር በፍፁም ሊምታታ አይገባውም፡፡
- የከተማው አስተዳደርም ሆነ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊው በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጪ ውይይታችን እንዳይካሄድ እንቅፋት በመሆናቸው ሕገ መንግሥታዊ የሆነውን የመሰብሰብ መብታችንን ለማስከበር ከተማ አስተዳደሩ የፈፀመው ድርጊት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች መሰረት ሕገ ወጥ መሆኑ እንዲወሰንልን እንዲሁም ውይይት እንዳናደርግ የሰጠውን ትዕዛዝ እንዲያነሳ እና ከዚህ በኋላ እንደዚህ አይነት ተግባር መፈጸም እንደማይችል እንዲታዘዝልን የክስ አቤቱታ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማስገባታችንን እናሳውቃለን፡፡
- የሕዝብና የመንግሥት ተቋማት የፓርቲን እና የመንግሥትን ተግባራትን በለየ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ፤ ለሕግ የበላይነት እና ፍትህ መረጋገጥ እንጂ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ላለ ፓርቲ የአገዛዝ መሳሪያ እንዳይሆኑ አበክረን ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡
- በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዝርጋታው ውስጥ በታማኝነት እና ሀገርን በማስቀደም መንፈስ መስራታችንን አጠናክረን የምንቀጥል ሲሆን የመንግሥት ሥልጣን የያዘው አካል ያንን ለመሸርሸር በሚሠራበት ጊዜ ሁሉ በምንም ዓይነት የማንታገስ እንደሆነ እና ባሉት ሰላማዊ እና ሕጋዊ አማራጮች በሙሉ የምንታገል መሆናችንን ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

ለሀገር ሰላም እና ለሕዝብ ደህንነት መከበር መቆማችንን የምንናገረውንም ሆነ የምንሠራውን ሌሎች እንዲወስኑልን ከመፍቀድ እና ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን አሳልፎ ከመስጠት ጋር በፍፁም ሊምታታ አይገባውም።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከአምባገነን ሥርዓቶች መፈራረቅ ተላቀን በእኩልነት እና በፍትህ ላይ የተመሰረተ አንድነታችንን ማረጋገጥ የሚችል እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት የሚያስችል ዕድል በሕዝብ ትግል እና መስዕዋትነት አግኝተን ዕድሉን በአግባቡ ለመጠቀም እና በሀገራችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ጠንካራ መሰረት ላይ ለማቆም አስቸጋሪ እና ከባድ ሂደት እያለፍን እንደሆነ ይታወቃል። ይህን ሂደት ከባድ እና አስቸጋሪ የሚያደርጉት ብዙ እንቅፋቶች መኖራቸው የሚጠበቅ ነው። በዋነኛነት ዘውግ ላይ ያተኮረው ፖለቲካ እና ትርክት በዜጎች መካከል የፈጠረው አለመተማመን እና የጥላቻ ስሜት፣ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በሚል አመለካከት እንዲሁም ከረጅም ጊዜ ሀገራዊ ጥቅም ይልቅ በአጭር ጊዜ የሚገኝ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በማሰብ ፍፁም ኃላፊነት በጎደለው መልኩ የሚደረጉ ቅስቀሳዎች፣ በከፍተኛ ቁጥር ከየትምህርት ተቋማቱ ትምህርት ጨርሰው ሥራ እየፈለጉ ላሉ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር አለመቻሉ የሚፈጥረው የተስፋ መቁረጥ ስሜት፣ እና በተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉ ሥርዓት አልበኝነቶች፤ የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመፍጠር የሚደረገውን ጉዞ ከባድ እና አስቸጋሪ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ይገኛሉ።

ከላይ ከተዘረዘሩት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመስረት እያደረግነው ያለውን ሂደት ከባድ ካደረጉት ምክንያቶች ባልተናነሰ ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ችግሮቹን መፍታት ወይንም ቢያንስ አለማባባስ የሚፈልገውን የኃላፊነት ስሜት እና ብቃት በሚገባ አለመረዳቱ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የመመስረት ሂደቱን የበለጠ አስቸጋሪ እና ውስስብ እያደረገው ይገኛል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በሀገራችን ከረጅም ጊዜ አምባገነናዊ ሥርዓቶች መፈራረቅ በኋላ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚደረገው ሽግግር ከፍተኛ ትዕግስት እና አርቆ አሳቢነትን እንደሚሻ በማመን እንደሀገር ባለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ ምክንያት በየጊዜው ከሚፈጠሩ ችግሮች ይልቅ የረጅም ጊዜ ሀገራዊ ግባችንን ማሳካት የምንችልበት ሂደት ላይ አትኩሮ ሲሠራ መቆየቱ ይታወቃል። ኢዜማ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በሙሉ ሰላማዊ፣ ሕጋዊ እና የሌሎችን መብት ባከበረ መልኩ መሆኑ እና ችግሮች በሚያጋጥሙ ጊዜ ወደተካረረ መንገድ ከመሄድ ይልቅ በሰከነ ውይይት ችግሮችን ለመፍታት እንደሚጥርም በተግባር የተረጋገጠ ሀቅ ነው። ይህንን የምናደርገው ማንንም ለማስደሰት ብለን

ወይንም በሕግ ስለምንገደድ ብቻ ሳይሆን እንደፓርቲ ለራሳችን ያስቀመጥናቸው እሴቶች ስለሚያስገድዱን ጭምር ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ፥ በየጊዜው የሚፈጠሩት ችግሮች እና መንግሥት ለችግሮቹ እየሰጠ ያለው ምላሽ በረጅም ጊዜ ማሳካት የምንፈልገውን ግብ አደጋ ውስጥ እየከተተው እንደሚገኝ እያስተዋልን ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ሕገወጥ የመሬት ወረራ እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ኢፍትሃዊ ዕደላን አስመልክቶ በአምስት ክፍለ ከተሞች ያደረገነውን ጥናትና የደረሰንበትን ውጤት ነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም በጽሕፈት ቤታችን ለሕዝብ ይፋ ማድረጋችን ይታወሳል፡፡ በጊዜው የዳሰሳ ጥናት ውጤቱን አዲስ አበባ በሚገኘው ራስ ሆቴል የስብሰባ አዳራሽ ለማቅረብ እቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መመሪያ እና የኢፌዴሪ ሰላም ሚኒስቴር በፈጠሩት እክል ሪፖርቱን የተወሰኑ የሚዲያ አካላት ብቻ በተገኙበት በጽሕፈት ቤታችን ለመስጠት ተገደን እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ሕገ መንግሥታዊ እውቅና ያለውን መብታችንን ተጋፍተው የጥናት ውጤቱ ለሕዝብ እንዳይደርስ የፈጠሩት እክል ተቋማቱ ለሕግ የበላይነት መከበር እና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፍላጎት እና ቁርጠኝነት እንደሚጎድላቸው በግልፅ ያሳየ ነበር፡፡ ያወጣነውን ሪፖርት አንድም የመንግሥት ሚዲያ ሽፋን ለመስጠት ፍላጎት አለማሳየቱም ጥያቄ የሚያጭር ነው፡፡

በጥናቱ ሕገወጥ ድርጊታቸው እና የአስተዳደር ብቃታቸው ጥያቄ ምልክት ውስጥ የገባባቸው ግለሰቦችና ተቋማት ከተራ ፉከራና ከአንገት በላይ የሆነ ይቅርታ ውጪ የጥናት ውጤቱን ትክክለኝነት ሊያፈርስ የሚችል ሌላ ተጨባጭ ማስረጃ ወይንም ጥናት ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ ኢዜማ የደረሰባቸውን የጥናት ውጤቶች ለሚመለከታቸው የፍትህ ተቋማት «በወንጀል ይጣራልኝ» አግቤቱታ ያቀረበ ሲሆን አቤቱታው የቀረበላቸው ተቋማት ላስገባነው አቤቱታ ምንም ዓይነት ምላሽ እስካሁን አልሰጡም፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት እና በስሩ የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁለት ተቋማት ጥናቱን ስንጀምር ግብዓት የሚሆን መረጃ እንዲሰጡን፣ ቀጥሎም በጥናት የተደረሱባቸው ግኝቶች ላይ አስተያየታቸውን ሰጥተው ያዘጋጀነው ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት ብንጠይቃቸውም ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ ጥናቱን ለሕዝብ ይፋ ካደረግን በኋላ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር የከንቲባ ጽሕፈት ቤት በደረሰን ጥሪ መሰረት በሪፖርቱ ውስጥ በተነሱ ጉዳዮች ላይ አዲስ ከተሾሙት ምክትል ከንቲባ እና ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር አንድ ጊዜ ውይይት አድርገን ነበር፡፡ በውይይቱም ችግሮቹን በማጣራት የእርምት እርምጃ እንደሚወሰድ የከተማ አስተዳደሩ ቃል ገብቶ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተጨማሪ ውይይት ለማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር፡፡ ሆኖም ውይይቱ ከተደረገ በኋላ አሁንም ድረስ በጥናት ውጤቱ የተደረሰባቸው ሕገ ወጥ እና ኢፍትሃዊ ድርጊቶች እየተፈፀሙ ስለመሆናቸው የሚደርሱንን ጥቆማዎች ለመቀበልም ሆነ ድርጊቶቹን ለማስቆም የከተማ አስተዳደሩ ፍላጎት እንደሌለው የሚያሳዩ ድርጊቶችን እየፈፀመ ይገኛል፡፡

የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ የጥናት ውጤቱን ለሕዝብ ይፋ ከማድረግ በተጨማሪ በጉዳዩ ላይ የሚመለከታቸው አካላትን ያሳተፈ የውይይት መድረክ ለማዘጋጀት ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት መስከረም 15 ቀን 2013 ዓ.ም በፓርቲው ጽሕፈት ቤት ውይይቱን ለማድረግ ዝግጅት አጠናቆ ነበር። በውይይቱ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ የተደረገላቸው ባለድርሻ አካላት የከተማውን አስተዳደር እና በስሩ የሚገኙ የሚመለከታቸው ተቋማት፣ በመሬት ወረራው ተጎጂ ሆነናል የሚሉ አካላትን፣ የከተማውን ፖሊስ እና የደህንነት አካላትን፣ ከአዲስ አበባ ዙሪያ ያለበቂ ካሣ ተነስተን በስማችን ለሌሎች አካላት ቤቶች ተሰጥተዋል የሚሉ አርሶ አደሮች ነበሩ።

የመጀመሪያ ውይይቱን መስከረም 15 ቀን 2013 ዓ.ም ለማካሄድ ዝግጅታችንን አጠናቀን ባለንበት ሰዓት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላም እና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ከመስከረም 15 በኋላ ባሉ ተደራራቢ በዓላት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የሥራ ጫና ውስጥ እንደሚገኝ ባደረሰን ጥቆማ መሰረት ተነጋግረን ውይይቱን ለመስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም አስተላልፈናል። የውይይት ቀን መቀየራችንን ለፀጥታ አካላት፣ ለከተማ አስተዳደሩ እና ለሌሎች የፓናል ውይይቱ ተሳታፊዎች በቁጥር ኢዜማ/036/13 በመስከረም 14 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አሳውቀናል።

በዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም፣ ሰላም እና ደህነነት እንዲሁም የሀገር ሉዓላዊነት ምንግዜም ቅድሚያ ይኖረዋል ለሚለው መርኻችን ያለንን ቁርጠኝነት በግልፅ አሳይተናል።

ይሁን እንጂ በታቀደው ቀን እና ሰዓት ውይይቱን እንደምናደርግ መረጃው የነበረው የከተማው አስተዳደር «የማጥራት ሥራውን አስተዳድሩ ባላጠናቀቀበት ወቅት ውይይት መጥራት ሌላ አተካራ እና ምናልባትም ወደግጭት የሚወስድ በመሆኑ የጠራችሁት ውይይት እንዲሰረዝ እንድታደርጉ እናሳስባለን። » በማለት በደብዳቤ ቁጥር አአ/ከፅ/03/03/23 በከንቲባ ጽሕፈት ቤት በኩል በላከልን ደብዳቤ አሳውቆናል፡ ፡ ይህ ደብዳቤ እኛ ጋር መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም ከቀኑ 8፡30 ከመድረሱ በፊት አስቀድመው የከተማ አስተዳደሩ ኃላፊዎች ውይይቱን እንድንሰርዝ በስልክ ጥሪ እና በአጭር መልዕክት የተለያየ ሙከራ ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆን ደብዳቤው ሲደርሰን ግን ደብዳቤው ቀድሞ የተጻፈ ለማስመሰል የደብዳቤው ቀን መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም በሚል ነበር። ከዚህ ውጭ በጉዳዩ ላይ በአካል ተገናኝቶ ለመወያየት የሚያስችል ዕድልም አላገኘንም። ከዚህም በተጨማሪ ይህ በከተማ አስተዳደሩ የተጻፈ ሕገወጥ ደብዳቤ ለፌደራል ፖሊስ፤ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ግልባጭ መደረጉ ከተማ አስተዳደሩ ለሕገወጥ ተግባሩ ተጠሪነታቸው እና ታማኝነታቸው ለሕዝብ እና ለሕገ መንግስቱ የሆኑትን ተቋማት መጠቀሚያ ለማድረግ ያለውን እኩይ ፍላጎት በግልፅ የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል።

ይህ የከተማ አስተዳደሩ ድርጊት ዓይን ያወጣ ሕገ ወጥነት ቢሆንም እና ውይይቱን የማድረግ ሙሉ ሕገ መንግሥታዊ መብት እንዳለን ብናምንም አላስፈላጊ ፍጥጫ ውስጥ ከመግባት ይልቅ ያሉት

ሕጋዊ አማራጮችን በመጠቀም መብታችንን ማስከበር እንዳለብን፣ የሕግ ተቋማትም ያላቸውን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችሉ ዕድል መስጠት አለብን ብለን በማመን ውይይቱን እንደገና ለማራዘም ወስነናል። በዚህም ምክንያት መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የሚደረግ የመሬት ወረራ እና ኢፍትሃዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕደላ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ልናደርግ የነበረው ውይይት ሳይደረግ ቀርቷል። ይህን መሰል ድርጊቶች ለሀገራችን ሕልውና ማንሰራራት መሰረት ለሆነው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ትልቅ ተግዳሮት የሚፈጥሩ ናቸው።

ለሀገር ሰላም እና ለሕዝብ ደህንነት መከበር መቆማችንን እንዲሁም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ የምንወስዳቸው እርምጃዎች የምንናገረውንም ሆነ የምንሠራውን ሌሎች እንዲወስኑልን ከመፍቀድ እና ሕገ መንግሥታዊ መብታችንን አሳልፎ ከመስጠት ጋር በፍፁም ሊምታታ አይገባውም። የከተማው አስተዳደር ችግሩን እፈታበታለሁ ባለው መንገድ ከመሄድ ባለፈ ለሌሎች ሕጋዊ ዕውቅና ላላቸው እና ሰላማዊ ለሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህን አድርጉ ይህን አታድረጉ የማለት የሕግም ሆነ የሞራል ሥልጣን የለውም። ኢዜማ እንዲህ ዓይነቱን ሕገወጥነት እና ለዘመናት ስንታገለው ወደቆየነውን የአፈና ሥርዓት ለመመለስ የሚደረግ ጥረትን በግልፅ ያወግዛል። ይታገላልም።

በተለይ የሕዝብና የመንግሥት ተቋማት የፓርቲን እና የመንግሥትን ተግባራትን በለየ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ፣ ለሕግ የበላይነት እና ፍትህ መረጋገጥ እንጂ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ላለ ፓርቲ የአገዛዝ መሳሪያ እንዳይሆኑ አበክረን ለማሳሰብ እንወዳለን። ይህ ወቅት ተቋማቱና መሪዎቻቸው ለሕግ የበላይነት እና ፍትህ በመቆም የተቋማቸውን ቅቡልነት እና በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን አመኔታ ለመጨመር እንዲሁም የግል ታሪካቸውን በክብር ለማስጠራት ምቹ አጋጣሚ ነው። ይሁን እንጂ ካለፈውም ይሁን ከቅርብ ታሪካችን ትምህርት ሳይወስዱ በአንድ ፓርቲ ወገንተኝነት የመቀጠል አዝማሚያ የተቋማቱን መልካም ስምና ተአማኒነት የሚያጠለሽ፣ ተቋማቱን እንድትመሩ እድሉን ያገኛችሁ ግለሰቦችም በሕግና በታሪክ ፊት የሚያስጠይቃችሁ እና የሚያስወቅሳችሁ መሆኑን ልትገነዘቡት ይገባል።

ኢዜማ ከሕጋዊ እና ሰላማዊ የፓለቲካ ትግል ውጪ አማራጭ የለውም። በእነዚህ አንኳርና መሰረታዊ ማዕቀፎች ውስጥ በመሆን በሚያደርገው እንቅስቃሴ ግን በየደረጃው ያሉ የገዢው ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚዎችንም ሆነ የመንግሥት ተቋማት ኃላፊዎችን ፊት እያየ ወይንም ፍላጎት እየጠበቀ የሚሠራ ድርጅት አለመሆኑ በግልፅ ሊታወቅ ይገባል።

በመሆኑም የከተማው አስተዳደርም ሆነ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊው በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጪ ውይይታችን እንዳይካሄድ እንቅፋት በመሆናቸው በሕገ መንግሥታዊ የሆነውን የመሰብሰብ መብታችንን ለማስከበር ከተማ አስተዳደሩ የፈፀመው ሕገ ወጥ ድርጊት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች መሰረት ሕገ ወጥ መሆኑ እንዲወሰንልን እንዲሁም ውይይት እንዳናደርግ የሰጠውን ትዕዛዝ እንዲያነሳ እና ከዚህ በኋላ እንደዚህ አይነት ተግባር መፈጸም እንደማይችል

እንዲታዘዝልን የክስ አቤቱታ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማስገባታችንን እናሳውቃለን።

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዝርጋታው ውስጥ በታማኝነት እና ሀገርን በማስቀደም መንፈስ መሥራታችንን አጠናክረን የምንቀጥል ሲሆን የመንግሥት ሥልጣን የያዘው አካል ያንን ለመሸርሸር በሚሠራበት ጊዜ ሁሉ በምንም ዓይነት የማንታገስ እና ለማስተካከል ባሉት ሰላማዊ እና ሕጋዊ አማራጮች በሙሉ ትግል የምናደርግ መሆኑን ለማስገንዘብ እንወዳለን። በአንጻሩ በሕግ አግባብ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በሚያግዝ እና የሀገር ሰላምና አንድነትን ለማስጠበቅ በሚደረግ ማናቸውም እንቅስቃሴ ከመንግሥት ጋርም ሆነ ከሌሎች የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ኃይሎች ጋር ሁሌም ተባብረን ለመሥራት ዝግጁ መሆናችንን በዚሁ አጋጣሚ መግለጽ እንፈልጋለን።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

መስከረም 29 ቀን 2013 ዓ.ም